# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2015/25*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

## የኃይል ለአፍሪካ ውጥን ኢትዮጵያ ከግሉ ዘርፍ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የምትፈጽመውን ታሪካዊ የኃይል ግዥ ስምምነት መፈረሙን አስታወቀ

**አዲስ አበባ፤ኢትየጵያ፤ ሐምሌ 23 ቀን 2007 ዓ. ም.፡-**ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ኢትዮጵያን በጎበኙበት በዚህ ሳምንት  የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ኮርቤቲ ጂኦተርማል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ከግሉ ዘርፍ የኃይል አቅራቢ ለመጀመሪያ ጊዜ በፈፀመችው የግዢ ስምምነት፤ ከኩባንያው ወደ 500 ሜጋ ዋት የሚጠጋ ንጹህ የጂኦተርማል ኤሌክትሪክ ኃይል ታገኛለች፡፡ በዚህ በኮርቤቲ የጂኦተርማል የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ፕሮጀክት ላይ የሚሳተፉ ባለሀብቶች የኃይል ለአፍሪካ አጋር የሆኑት ሬይክጃቪክ ጂኦተርማል እና በርክሌይ ኢነርጂ፤እንዲሁም አይስላንድ ድሪሊንግ ናቸው፡፡

በተጨማሪም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ከሬይክጃቪክ ጂኦተርማል ጋር ከዚህ ቀደም ባደረገው ስምምነት መሠረት በቱሉ ሞዬና በአባያ አካባቢዎች ተጨማሪ 500 ሜጋ ዋት ማመንጫዎችን እንዲገነባ የመግባቢያ ሰነድ ለመፈረም በድርድር ላይ ይገኛል፡፡ በነዚህ ሁለት ስምምነቶች ብቻ ኢትዮጵያ ለሁለት ሚሊዮን አባወራዎች በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል ሊሰጥ የሚችል የ1,000 ሜጋ ዋት ተጨማሪ አቅም ይኖራታል፡፡

የአሜሪካ ኩባንያ የሆነው ሬይክጃቪክ ጂኦተርማል ላለፉት በርካታ ዓመታት በነዚህ ሦስት የጂኦተርማል ኃይል ማመንጫ ቦታዎች ለሚያከናውናቸው የፕሮጀክት ሥራዎች መነሻ የሚሆኑ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በቀጣይ ከ8-10 ባሉ ዓመታት ውስጥ የሚኖረው አጠቃላይ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ከ4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚልቅ የሚገመት ሲሆን፤እስካሁን መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በዚህ ዘርፍ በአፍሪካ ደረጃ ካፈሰሱት መዋዕለ ንዋይ በእጅጉ የላቀም ይሆናል፡፡ ከኮርቤቲ ጋር የተደረሰው ስምምነት ብቻውን በአፍሪካ ደረጃ መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት ከተደረጉ ማናቸውም የኃይል ማመንጫ ስምምነቶች በእጥፍ የሚበልጥ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

እነዚህ የጂኦተርማል ኃይል ፕሮጀክቶች ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነትን በ30,000 ሜጋ ዋት እና 60 ሚሊዮን የኤሌክትሪክ መሥመሮችን ለማገናኘት ያለመው የፕሬዚዳንት ኦባማ የኃይል ለአፍሪካ ውጥን አካል ናቸው፡፡

ሰኞ ዕለት ፕሮዚዳንት ኦባማ ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ጋር የጋራ መግለጫ በሰጡበት ወቅት፤ የኮርቤቲ ፕሮጀክት የግሉ ዘርፍ የኤሌክትሪክ አቅምንና ሌሎች ለኢኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ መዋቅሮችን በመገንባት ረገድ ለሚጫወተው ሚና ትልቅ ማሳያ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ የ500 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭም ሆነ በጉጉት የሚጠበቀው የሁለተኛው ዙር የ500 ሜጋ ዋት አቅም ማሳጊያ የመግባቢያ ሰነድ ፊርማ በረጅም ጊዜ ለሚከናወኑና አቅም ፈጣሪ የሆኑ ፕሮጀክቶችን ለማካሄድ መሠረት የሚጥሉ ናቸው፡፡

POWER AFRICA

ፕሬዚዳንት ኦባማ በጋራ ጋዜጣዊ መግለጫው ወቅት ሲናገሩ፣"የኢትዮጵያን የጂኦተርማል ኃይል አቅም ለመገንባት ሀገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ከግሉ ዘርፍ ጋር በሚደረስ ስምምነት ያላት እምቅ ኃይል ሥራ ላይ መዋል እንዲችል በጋራ በመሥራት ላይ እንገኛለን። ይህም መንግሥት በመላው ኢትዮጵያ በከፍተኛ ደረጃ የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነትን ለማሳደግ የያዘውን ሰፊ ግብ እንዲሁም ሀገሪቱ በታዳሽ የኃይል ዘርፍ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የገበያ ዕድልን መፍጠር እንድትችል ያግዛታል " ብለዋል።

የኃይል ለአፍሪካ ውጥን ከተጀመረበት ከ2005 ዓ.ም. ጀምሮ ለኢትዮጵያ መንግሥት ከተደረጉ ድጋፎችና ከተመቻቹ ሁኔታዎች መካከል በአፍሪካ ልማት ባንክ የአፍሪካ የህግ ድጋፍ አገልግሎት በኩል በሚደረጉ ድርድሮች ላይ ያተኮረ የህግ ድጋፍ፤ለኃይል ሽያጭና ለአፈጻጸም ስምምነቶች ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፤ለኢትዮጵያ መንግሥት በፋይናንስ ሞዴል፣በጂኦተርማል ኃይል ማከማቻዎችን በመፈተሽ፣እንዲሁም በጂኦተርማል የኃይል ምንጭ ዙሪያ ለሚደረጉ የቁጥጥር ሥራዎች ሙያዊ ድጋፍ መስጠት ይገኙባቸዋል። የኃይል ለአፍሪካ ውጥን ዋና ዓላማ ለአንድ ለተወሰነ ፕሮጀክት ድጋፍ ማድረግ ሳይሆን፤በቀጣይ ዓመታት በግሉ ዘርፍ ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች የመንግሥትን የተሻለ የመደራደር አቅም በመፍጠር ላይ ያተኮረ ነው።

የሬይክጃቪክ ጂኦተርማል ሥራ አስኪያጅ  የሆኑት ማይክል ፊሊፐ በበኩላቸው፣"ይህ ታሪካዊ የሆነ ስምምነት እንዲጠናቀቅ ላደረጉ የኢትዮጵያ መንግሥት ሚኒስትሮችና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሥራ አስፈጻሚዎች ላቅ ያለ ምስጋና እናቀርባለን። የአሜሪካ መንግሥት የኃይል ለአፍሪካ ውጥን ያበረከተው አስተዋጽኦም በጣም የሚደነቅ ነው። ኃይል ለአፍሪካ ለኢትዮጵያ መንግሥት ተደራዳሪ አካላት ከሰጠው ቀጥተኛ ድጋፍ በተጨማሪ፤እንደ ኮርቤቲ ያሉ በአፍሪካ ለሚደረጉ የኤሌክትሪክ ኃይል የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች ፤በዘርፉ የተሰማሩ በአሜሪካም ሆነ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ተቋማትን ደረጃ ከፍ በማድረግ የአክሲዮን ወጪያቸው በእጅጉ ዝቅ እንዲል አድርጓል።"

###

POWER
AFRICA